# የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት

# ደቡብ ኢትዮጵያ ነጋሪት ጋዜጣ

# DEBUB ETHIOPIA NEGARIT GAZETA

# OF THE SOUTH ETHIOPIA REGIONAL STATE

፪ኛ ዓመት ቁጥር ፳፩
አርባ ምንጭ ታህሳስ ፰ ቀን ፪ሺ፲፮ዓ.ም

በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2nd Year No 21
Arba Minch December, 2023


## አዋጅ ቁጥር ፳፬/፪ሺ፲፮ ዓ.ም

## የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የግብርና ሥራ ገቢ ግብር አዋጅ

### መግቢያ

መንግስት ለአርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ ምርት ዕድገት አስተዋጽኦ ያላቸውን ግብዓቶች በወቅቱ በማቅረብ እንዲሁም የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ አርሶ አደሩ እና አርብቶ አደሩ የገበያ መር የግብርና አመራረት ዘዴን እንዲከተሉና እንዲሁም ምርትና ምርታማነትን እንድያሳድጉ ማድረግ በማስፈለጉ፤

በክልሉ በተነጻጻሪ በትንሽ መሬት ብዙ ምርት ማምረት እንዲሁም የእንስሳት ሀብትና ልማት ማሳደግ የሚቻልበት ዕድል የተፈጠረ ከመሆኑም በላይ የአርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ የኑሮ ዘይቤ እየተሻሻለ በመምጣቱ፣

## Proclamation No. 24/2023

## Rural Land Use Fee and Agricultural Income Tax Proclamation of the South Ethiopia Regional State

### Introduction

**WHEREAS**, it has become necessary that the government has to provide timely inputs that contribute to the growth of farmers' and pastoralists' production, as well as to encourage farmers and pastoralists to adopt market-oriented agricultural production methods through various supports to increase production and productivity;

**WHEREAS**, in the region, comparatively opportunities have been created to produce more products on a small amount of land, as well as to increase livestock and development, and the livelihoods of farmers and pastoralists are improving;

| | |
|---|---|
| በክልሉ የተለያዩ የመስኖ አማራጮች እየተስፋፉ በመምጣታቸው በመስኖ የሚያመርቱ አርሶ አደሮች ቁጥር እየጨመረ እና በዓመት ከአንድ ጊዜ በላይ የተለያዩ ምርቶችን በማምረት ዓመታዊ ገቢያቸው እያደገ በመምጣቱ፤ | **WHEREAS**, various irrigation options are expanding in the region, the number of farmers using irrigation and their annual income is increasing by producing various products more than once a year; |
| በመኸርና በመስኖ የሚያለሙ አርሶ አደሮች መካከል ያለውን ኢ-ፍትሀዊ የእርሻ ስራ ገቢ ግብር አከፋፈልን በማስተካከል አሁን ካለው የኢኮኖሚ ዕድገት መንግስት ተገቢውን ግብር መሰብሰብ በሚያስችል አኳኋን ህግ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤ | Fixing the unfair distribution of farm income tax between harvest and irrigated farmers and making it necessary to legislate in a manner that allows the government to collect appropriate taxes from the current economic growth; |
| በክልሉ ውስጥ በምግብ ዋስትና የታቀፉትን አርሶ አደሮች ካልታቀፉት አርሶ አደሮች በተመን ለይቶ የመሬት መጠቀሚያ እና የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር ማስከፈል በማስፈለጉ፣ | Farmers in the region who are food insecure are excluded from the need to pay land use and farm income taxes; |
| ግብርና ለክልሉ የምርት ዕድገት ከፍተኛ ድርሻ ያለው በመሆኑ ከዚህ ዘርፍ የሚሰበሰበው የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር ለክልሉ መንግስት ተገቢውን አስተዋጽኦ ሊያበረክት በሚችል መልኩ የክፍያ መጠን መወሰን በማስፈለጉ፣ | Since agriculture plays a significant role in national production growth, it is necessary to determine the amount of payment in such a way that the rural land utilization fees and farm income tax collected from this sector can contribute adequately to the state government; |
| የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ምክር ቤት በክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፬ ንዑስ አንቀጽ ፫/ሀ/ መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል። | The South Ethiopia Regional Council issued this proclamation pursuant to Article 54, Sub-Article 3/a/ of the Regional Constitution. |
| **ክፍል አንድ**<br>**ጠቅላላ ድንጋጌዎች** | **Part One**<br>**General Provisions** |
| ፩. አጭር ርዕስ<br>ይህ አዋጅ "**የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የግብርና ሥራ ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፳፬/፪ሺ፲፮**" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል። | **1.Short Title**<br>This Proclamation may be cited as "the **Rural Land Use Fee and Agricultural Income Tax Proclamation No. 24/2023**" |

| | |
|---|---|
| **፪. ትርጓሜ** | **2. Definitions** |
| በዚህ አዋጅ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር ፦ | In this Proclamation, unless the context requires otherwise**:** |
| ፩፥ **"ክልል"** ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ነው፤ | **1) "Region"** means the South Ethiopia Region; |
| ፪፥ **"ቢሮ"** ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ገቢዎች ቢሮ እና እንደአግባብነቱ በየአስተዳደር እርከኑ የሚገኙ መምሪያዎች፤ ጽ/ቤቶች እና የታክስ ማዕከላትን ይጨምራል፤ | 2) **"Bureau"** means the Revenue Bureau of the South Ethiopia Region as well as the departments and office at each administrative level; |
| ፫፥ **"የገጠር መሬት"** ማለት በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በገጠር አስተዳዳር ወሰን የተጠቃለለ የገጠር መሬት ይዞታ እና በከተሞች አስተዳዳር ፕላን ወሰን ክልል ውስጥ ያለ አርሶ አደር ለእርሻ ሥራ አገልግሎት የሚጠቀምበት መሬት ወይም በየትኛውም አከባቢ በአርሶ አደር ይዞታ ስር የሚገኝ መሬት ነው። | **3) "Rural land"** means land used by a farmer for agricultural purposes within the boundaries of the Rural Administrative Plan and within the boundaries of the Urban Administrative Plan in the South Ethiopia Region, or land under the ownership of a farmer in any area in the Region. |
| ፬፥ **"አርሶ አደር"** ማለት የራሱንና የቤተሰቦቹን መሠረታዊ ፍላጐቶችን ለማሟላትና ተጨማሪ ገቢ ለማግኘት የእርሻ ሥራ የሚያካሂድ ማንኛውም ሰው ነው። | **4) "Farmer"** means any person who engages in agricultural activities to meet the basic needs of himself and his family and to earn additional income. |
| ፭፥ **"አርብቶ አደር"** ማለት የራሱንና የቤተሰቦቹን መሠረታዊ ፍላጐትና ተጨማሪ ገቢ ለማግኘት በከብት እርባታ ሥራ የሚተዳደር ማንኛውም ሰው ነው። | **5) "Pastoralist"** means any person who engages in livestock farming to meet his or her family's basic needs and to earn additional income. |
| ፮፥ **"የንግድ የግብርና ሥራ"** ማለት ደጋ ወይም ወይና ደጋ በሆኑ አከባቢዎች አንድ ሰው በያዘው ከ7 ሄክተር በላይ እና በቆላማ ቦታ ደግሞ አንድ ሰው በያዘው ከ10 ሄክተር በላይ የሆነ ገጠር መሬት ላይ የሚከናወን የግብርና ሥራ ነው። | 6) **"Commercial agricultural activity"** means agricultural activity carried out on more than 7 hectares of rural land occupied by a person in highland or plateau and in lowland areas more than 10 hectares owned by a person. |
| ፯፥ **"የግብርና ሥራ ገቢ ግብር"** ማለት የመሬት ይዞታን መጠን ወይም ከእንስሳት የሚገኘን ገቢ መሰረት በማድረግ ከግብርና ሥራ በሚገኝ ገቢ ላይ በዚህ አዋጅ መሰረት በቁርጥ ተወስኖ በአርሶ አደር ወይም በአርብቶ አደር የሚከፈል ግብር ነው። | **7) "Agricultural Income Tax"** means a tax levied on income derived from agricultural activities based on the size of land holdings or income derived from livestock, as determined in accordance with this Proclamation, and paid by farmers or herders; |
| ፰፥ **"የመሬት ይዞታ"** ማለት በክልሉ በአንድ አካባቢ ወይም በተለያዩ ቦታዎች ሆኖ በአርሶ አደር | 8) **"Land holding"** means rural land that is registered as a possession in the name of a farmer |

ወይም በአርብቶ አደር ስም በይዞታነት የተመዘገበና የጓሮ መሬትን ጨምሮ ለማናቸውም የግብርና ልማት ሥራዎች የተያዘ የገጠር መሬት ነው፤

፱፦ **“የመሬት ኪራይ ክፍያ”** ማለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት ማንኛውም የመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም የግል ባለሃብት በክልሉ የሚገኝ የገጠር መሬት ለንግድና ኢንቨስትመንት ልማት ተግባር በሊዝ ተከራይቶ አግባብ ባለው ሕግና በውል ስምምነት በተወሰነው ምጣኔ መሠረት ለመሬቱ ኪራይ በየዓመቱ የሚከፍለው የሊዝ ክፍያ ነው፤

፲ **“የመጠቀሚያ ክፍያ”** ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በክልሉ አርሶ አደር እና አርብቶ አደር የሚከፈል የገጠር መሬት መጠቀሚያ ዓመታዊ ክፍያ ነው፡፡

፲፩ **“በምግብ ዋስትና የታቀፉ ቀበሌዎች”** ማለት የክልሉ መንግስት በሚያወጣው የምግብ ዋስትና መርሀ ግብር በታቀፉ ቀበሌዎች የሚኖሩ አርሶ አደሮች የሚገኙበት ነዉ፡፡

፲፪ **“በመደበኛ እርሻ ተጠቃሚ”** ማለት በይዞታው ወይም በተከራየው የእርሻ መሬት ላይ የዝናብ ወቅትን ብቻ ጠብቆ ከዓመታዊ ሰብሎች ምርት በመሰብሰብ የሚጠቀም አርሶ አደር ማለት ነው፡፡

፲፫ “በመስኖ እርሻ ተጠቃሚ” ማለት ባለው የይዞታ የእርሻ መሬት ላይ የመስኖ ቦይ በባህላዊ ወይም በዘመናዊ መንገድ ወደ ማሳ በማስገባት ከመደበኛው የዝናብ ወራት ከሚመረት ሰብል በተጨማሪ በሌሎች ወቅቶች በዓመት ከአንድ በላይ በሆነ ጊዜ በማልማት የሚጠቀም አርሶ አደር ነው፤

፲፬ “ግብር ሰብሳቢ” ማለት የቀበሌው አስተዳደር ወይም የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የግብርና ሥራ ገቢ ግብር እንዲሰበስብ በሚመለከተው የቀበሌ አስተዳደር የሚወከል ሰው ነው፡፡

፲፭ “የሕብረት ሥራ ማህበር” ማለት በሕብረት ሥራ ማህበራት ማቋቋሚያ ሕግ መሠረት በግብርና ሥራ የተደራጀ የሕብረት ሥራ ማህበር ነው፡፡

or pastoralist in one area or in different areas of the region and reserved for any agricultural development activities, including backyard land;

9) **“Land rental payment”** means the annual lease payment for the land leased by any government development organization or private investor in the region for commercial and investment development purposes, in accordance with sub-article 6 of this article, at the rate determined by the relevant law and the contract;

10) **“Usage Fee”** means the annual rural land use fee paid by farmers and pastoralists of the region in accordance with this Proclamation;

11) **"Kebeles covered by Food security"** mean farmers living in kebeles embraced by the regional government's food security program**;**

12) **"Beneficiary of Regular farmer"** means a farmer who harvests the product of annual crops on his owned or leased agricultural land only on the rainy season:

13) **"Beneficiary of irrigated farming"** means a farmer who uses irrigation canals, either traditional or modern, on his agricultural land to cultivate crops more than once a year, other than those grown during the regular rainy season;

14) **"Tax collector"** means a kebele administration or a person represented by the relevant Kebele administration to collect rural land use fee and agricultural income tax.

15) **"Cooperative"** means a cooperative society organized for agricultural purposes in accordance with the Cooperative Societies Establishment Law.

፲፮ የዘገየ ክፍያ" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 በተገለጸው ቀንና ወር ውስጥ ያልተከፈለ የግብርና ሥራ ግብር እና የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ ነው፡፡

፲፯ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ወይም የሕግ ሰውነት የተሰጠው አካል ነው፡፡

## ፫. የተፈፃሚነት ወሰን

፩. ይህ አዋጅ ተፈፃሚ የሚሆነው በክልሉ ውስጥ በግብርና ሥራ በተሰማሩ ሰዎች የሚሰበሰበውን የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የግብርና ሥራ ገቢ ግብር በሚመለከት ነው፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም በንግድ ግብርና ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች ከግብርና ሥራ በሚያገኙት ገቢ ላይ ግብር የሚከፍሉት በገቢ ግብር አዋጅ መሰረት ይሆናል፡፡

## 4. የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የግብርና ገቢ ግብር አጣጣል

፩፦ በእንያንዳንዱ አርሶ አደር ይዞታ የሚገኘው መሬት በምግብ ዋስትና የታቀፈ እና ያልታቀፈ በሚል በሁለት ምድብ ተከፍሎ የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ የሚከፈልበት ይሆናል፡፡

፪፦ አርሶ አደሮች በዝናብ ውሃ በመጠቀም ምርት የሚያመርቱ፣ መስኖ በመጠቀም የሚያመርቱ በሚል በሁለት ምድብ ተከፍሎ የግብርና ስራ ገቢ ግብሩ በእያንዳንዱ ተለይቶ ከተሰላ በኋላ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተጠቀሰው ጋር በማዳመር ግብሩ የሚወሰን ይሆናል፡፡

፫፦ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተገለጸተው እንደተጠበቀ ሆኖ አከፋፈሉ

16) **Delayed payment"** means the tax on agricultural work and the rural land use fee that has not been paid during the day and month specified in Article 12 of this Proclamation.

17) **"Person"** means a natural or juridical person.

## 3. Scope of Application

1. This Proclamation shall apply in respect of agricultural income tax on the rural land use fee collected by persons engaged in agricultural activities in the region.
2. Notwithstanding the provisions of Article 1 of this Article, persons engaged in commercial agriculture shall pay taxes on their income from agricultural activities in accordance with the Income Tax Proclamation.

## 4. Rural Land Use Fees and Agricultural Income Tax

1. The land in the possession of each farmer will be divided into two categories: food security embraced and not embraced, which rural land use fee will be paid.
2. Farmers, who produce crops using rainwater and using irrigation, are divided into two categories and the income tax on agricultural activity shall be calculated separately in each and shall be added by the tax in sub article 1 of this article.
3. Without prejudice to the provisions of sub articles 1 and 2 of this Article, the collection of both types

ሁለቱም ገቢ አይነቶች በአንድ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ላይ በየራሳቸው ገቢ ኮድ በማስቀመጥና በማዳመር የሚሰበሰብ ይሆናል፡፡

፬÷ የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የግብርና ስራ ገቢ ግብር ስሌቱ በክልሉ ውስጥ በምግብ ዋስትና መርሃ ግብር የታቀፉና እና ያልታቀፉ በሚል በሁለት ምድብ ተለይቶ የሚሰላ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ አፈፃፀም

### ፭. የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያን ስለመክፈል

ማንኛውም የገጠር መሬት በይዞታው ስር ያለ ሰው መሬቱ በሚሰጠው ደረጃ መሰረት በማድረግ በያዘው የገጠር መሬት ይዞታ መጠን ልክ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት በየዓመቱ የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

### ፮ የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ ተመን

፩÷ በክልሉ የሚገኝ ማንኛውም በምግብ ዋስትና ያልታቀፈ አርሶ አደር በያዘው የገጠር መሬት ይዞታ ስፋት መጠን ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 1 በተመለከተው ማስከፈያ መጠን አመታዊ የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ ይከፍላል፡፡

፪÷ የክልሉ መንግስት በሚያወጣው የምግብ ዋስትና መርሃ ግብር የታቀፈ አርሶ አደር ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ 2 በተመለከተው የማስፈጸሚያ ምጣኔ የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ ይከፍላል፡፡

፫÷ የንግድ ግብርና ሥራ በሚያከናውኑ ሰዎች በይዞታቸው ስር ላለ መሬት የገጠር መሬት

of revenue shall be made by sorting and listing to their respective revenue codes on the same receipt.

4. Rural land utilization fees and agricultural income taxes will be calculated into two categories; food security embraced and not emraced.

## Part Two

## Rural Land Use Payment Execution

### 5. Rural Land Use Payment

Any person in possession of rural land shall be obliged to pay a rural land use fee annually in accordance with the provisions of this proclamation, based on size of the land.

### 6. Rural Land Use Fee Rate

1. Any farmer who is not embraced under food security program in the region shall pay an annual rural land use fee based the size of land at the rate specified in Table 1 of this Proclamation.
2. A farmer who is embraced in the Food Security Scheme, issued by the State Government, shall pay a rural land use fee at the implementation rate specified in Table 2 attached to this Proclamation.
3. Persons carrying out commercial agriculture shall pay a fee for the use of rural land on land under

መጠቀሚያ ክፍያ የሚከፍሉት ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ 3 በተመለከተው ማስከፈያ ምጣኔ መሰረት ይሆናል፡፡

፬፥ ብቻቸውን ቤተሰብ የሚያስተዳደሩ ሴት አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች የመሬት መጠቀሚያ ክፍያ የሚከፍሉት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1-3 ከተዘረዘረው እያንዳንዱ ማስከፈያ ምጣኔ 5% ዝቅ ባለ ማስከፈያ ምጣኔ ነው፡፡

## ክፍል ሦስት
## የግብርና ሥራ ገቢ ግብር አከፋፈል

### ፯. የግብርና ሥራ ገቢ ግብር ስለመክፈል

ማንኛውም አርሶ አደር ወይም አርብቶ አደር በተሰማራበት የግብርና ሥራ በየአመቱ ከሚያገኘው ገቢ ላይ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሰረት የግብርና ሥራ ገቢ ግብር ክፍያ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

### ፰. የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር ተመን

፩፥ ማንኛውም በምግብ ዋስትና ያልታቀፈ አርሶ አደር በየዓመቱ የግብርና ሥራ ግብር ክፍያ ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘ ሰንጠረዥ 4 በተመለከተው መሠረት የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

፪፥ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም የክልሉ መንግስት በሚያወጣው የምግብ ዋስትና የሚታቀፍ አርሶ አደር ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘ በሰንጠረዥ 4 በተመለከተው መሠረት በየዓመቱ የግብርና ሥራ ገቢ ግብር ይከፍላል፡፡

፫፥ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የንግድ ግብርና ሥራ የሚሰራ አርሶአደር በሚያገኘው ገቢ ላይ ግብር የሚከፍለው በገቢ ግብር አዋጅ መሰረት ይሆናል፡፡

their possession in accordance with the rate specified in Table 3 attached to this Proclamation.

4. Female farmers and pastoralists who run households alone, shall pay land use fees at a rate lower than 5% of each payment rate listed in sub-articles 1-3 of this Article.

## Part Three
## Agricultural Activities Income Tax Payment

### 7. Paying Agricultural Work Income Tax

Every farmer or pastoralist shall be obliged to pay agricultural income tax in accordance with this Proclamation on the annual income of the agriculture in which he is engaged.

### 8. Rate of Agricultural Work Income Tax

1. Any farmer, who is not covered in food security program, shall pay an annual agricultural tax as set out in Table 4 of this Proclamation.
2. Notwithstanding the provisions of Article 1 of this Article, a farmer who is subject to food security issued by the regional Government shall pay income tax annually in accordance with the provisions of Schedule 4 of this Proclamation.
3. Without prejudice to the provisions of Articles 1 and 2 of this Article, a farmer who engages in commercial agricultural activity shall pay taxes on his earnings in accordance with the Income Tax Proclamation.

፬÷ እንስሳትን በማርባት ሥራ ላይ የተሰማራ አርሶ አደር ወይም አርብቶ አደር ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ 5 በተመለከተው መሰረት የግብርና ሥራ ገቢ ግብር ይከፍላል፡፡

**፱. የእንስሳት እርባታ ገቢ ግብር ክፍያ ተመን**

፩÷ በአንቀጽ 11 በተጠቀሱት አካባቢዎች የሚገኝ ማንኛውም አርብቶ አደር የሚከፍለው ዓመታዊ የእንስሳት እርባታ ገቢ ግብር ተመን ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘ ሰንጠረዥ 5 በተመለከተው መሠረት ይሆናል፡፡

፪÷ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሱት እንስሳት እያንዳንዳቸው የሚሰጡት ጠቀሜታ ከሌላው ሲነፃፀር ያለው መጠን እኩሌታ የሚመዘንበት ዝርዝር አሠራር በደንብ ይወሰናል፡፡

**፲. በእርሻ ሥራ የተሰማራ አርብቶ አደር**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 የተመለከተው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በስሙ የተመዘገበ የመሬት ይዞታ ኖሮት ግማሽ ሄክታር ወይም ከዚያ በላይ ስፋት ባለው መሬት ላይ በማንኛውም የእርሻ ሥራ በተጨማሪነት ተሰማርቶ ምርት በመሰብሰብ ተጠቃሚ መሆን የቻለ አርብቶ አደር የመሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር የሚከፍለው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 እና 8 በተወሰነው ተመን መሠረት ይሆናል፡፡

**፲፩. የእንስሳት እርባታ የገቢ ግብር ተመን የሚመለከታቸው አካባቢዎች**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 የተደነገገውን የአርብቶ አደር የእንስሳት እርባታ የገቢ ግብር ተመን የሚመለከታቸው የክልሉ አካባቢዎች በደቡብ ኦሞ ዞን የሠላማጎ፣ የማሌ፣ የበናፀማይ፣ የዳሰነች፣

4. A farmer or pastoralist engaged in animal husbandry shall pay agricultural income tax as set out in Table 5 attached to this Proclamation.

**9. Rate of Animal husbandry Income Tax**

1. The annual Animal husbandry income tax rate payable by any pastoralist located in the areas covered in Article 11 shall be in accordance with the table 5 attached to this Proclamation.
2. The detailed procedure for determining the relative importance of each of the animals referred to in sub-Article 1 of this Article shall be determined by regulation.

**10. Pastoralist engaged agricultural activity**

Without prejudice to the provisions of Article 8 of this Proclamation, a pastoralist who has registered land ownership in his name and who is engaged in any agricultural activity on land measuring half a hectare or more and who is able to benefit from the harvest shall pay land use fee and agricultural income tax at the rates specified in Articles 6 and 8 of this Proclamation.

**11. Areas subject to Animal husbandry income tax rate**

The income tax rate for pastoral animal husbandry provided for in Article 9 of this Proclamation shall apply only to pastoralists in South Omo zone kebeles of Selamago, Male, Bena Tsemay, Dasenech, Nigatom

| | |
|---|---|
| የኛንጋቶምና በሐመር ወረዳዎች በሚገኙ ቀበሌዎች ውስጥ ነዋሪ የሆኑ አርብቶ አደሮች ብቻ ይሆናል፡፡ | and Hamer woredas of the region concerned. |
| **፲፪. የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የግብርና ሥራ ገቢ ግብር መሰብሰቢያ ጊዜ** | **12.The Rural Land Use Fee and Agricultural Income Tax Collection Period** |
| ፩፥ በዚህ አዋጅ የተጣለው የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የግብርና ሥራ ገቢ ግብር የሚሰበሰበው በበጀት ዓመቱ ከጥቅምት 1 ጀምሮ እስከ ሚያዚያ 30 ባለው ጊዜ ውስጥ ይሆናል፡፡ | 1. The rural land use fees and agricultural income tax imposed by this proclamation shall be collected between October 1 of the fiscal year and April 30. |
| ፪፥ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም አርሶ አደር በፈቃደኝነት በበጀት አመቱ መጀመሪያ የተጣለበትን የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ እና የግብርና ሥራ ገቢ ግብር መክፈል ይችላል፡፡ | 2. Without prejudice to the provisions of sub article 1 of this Article, any farmer may voluntarily pay the rural land settlement fee and agricultural income tax imposed at the beginning of the fiscal year. |
| ፫፥ ከመንግሥት የእርሻ ልማት ድርጅቶች እና በእርሻ ሥራ ላይ ከተሰማሩ የግል ባለሃብቶች የሚፈለገውን የገጠር መሬት ኪራይ ክፍያ የሚፈፀመው መሬቱን ሲረከቡ 50 በመቶ ቅድመ ክፍያ እና ቀሪው 50 በመቶ በውሉ ጊዜ በየዓመቱ ከጥቅምት 1 እስከ ሚያዚያ 30 ባለው ጊዜ ወስጥ መክፈል ይኖርበታል፡፡ | 3. The land use fee payment required from the state farming organizations and private agricultural investors shall be paid 50% of the total amount as down payment while they take over the rural land and the other remaining 50% on installment base annually through out the lease period from October 1 to April 30 of every year. |
| **፲፫. የአርሶ አደሩ ግዴታ** | **13. Obligation of the Farmer** |
| ፩፥ ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ማንኛውም አርሶ አደር ያለውን ትክክለኛ የመሬት ይዞታ ልክ በእጁ ላይ በሚገኘው የይዞታ ማረጋገጫ ሠርተፍኬት በተመለከተው መጠን መሠረት ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ላይ በሚገልፀው አኳኋን በየዓመቱ ከሐምሌ 15 በፊት ለቀበሌው አስተዳደር የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡ | 1. For the implementation of this proclamation, any farmer is obliged to inform the kebele administration of his actual land holdings, as per the land tenure certificate in his possession, before July 15 of each year, in accordance with the directives issued by the Bureau. |

፪፥ ማንኛውም አርሶ አደር በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 እና 8 የተወሰነውን የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር በአንቀጽ 12 በተገለፀው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለግብር ሰብሳቢው በደረሰኝ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

**፲፬. የአርብቶ አደሩ ግዴታ**

፩፥ ለግብሩ አወሳሰን ቀናነት ሲባል ማንኛውም አርብቶ አደር በባለቤትነት የያዛቸው ትክክለኛው የእንስሳት ሃብት የቀንድ ከብቶች፣ ግመሎች እና ሌሎች እንስሳት ብዛት ልክ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ላይ በሚገለፀው አኳኋን መሠረት በየዓመቱ ከነሐሴ 15 በፊት ለቀበሌው አስተዳደር ወይም የአርብቶ አደር ተወካዮች ላሉበት የቀበሌ ገማች ኮሚቴ በየጊዜው በማሳወቅ ግብሩን እንዲወሰን የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

፪፥ ማንኛውም አርብቶ አደር በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 የተወሰነውን ግብር በአንቀጽ 12 በተገለጸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለግብር ሰብሳቢው በደረሰኝ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል አራት

## የአስፈፃሚ እና የግብር ሰብሳቢ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

**፲፭. የቀበሌ አስተዳደር ተግባርና ኃላፊነት**

፩፥ በቀበሌው ም/ቤት ጉባኤና በተለያዩ የሕዝብ መድረኮች የአዋጁን አስፈላጊነት፣ ዓላማና ጠቀሜታ ለሕብረተሰቡ በማሳወቅ አርሶ አደሩና

2. Any farmer shall be obliged to pay the rural land use fee and agricultural income tax specified in Articles 6 and 8 of this Proclamation to the tax collector within the time limit specified in Article 12.

**14. Obligation of the pastoralist**

1. Any pastoralist shall have the obligation to declare the actual number of cattle of domestic horn animals, camels and other animals owned currently to the Kebele Administration or Estimating Committee which include representatives of pastoralists and kebele officials periodically before August 23, according to the condition stated on the directive that will be issued by the Bureau, for the proper assessment of payable tax.

2. Any pastoralist shall have the obligation to pay tax to the tax collector according to Article 9 of this proclamation in the period of time mentioned in Article 12 of this proclamation.

## Part Four

## Power and Functions of executive and tax collecting bodies

**15. Power and Functions of Kebele Administration**

1. It shall communicate the importance, purpose, and significance of the proclamation to the public at the Kebele Council and various public

አርብቶ አደሩ በአዋጁ የተጣለበትን ግዴታ ለይቶ በመገንዘብ በአግባቡ እንዲፈፀም ማስቻል አለበት፡፡

፪፥ እያንዳንዱ አርሶአደርና አርብቶአደር ያስታወቀውን የመሬት ይዞታ መጠን ወይም የእንስሳት ልክ መረጃ ትክክለኛነት አመሳክሮና አረጋግጦ ለወረዳው አስተዳደር ይገልፃል፡፡

፫፥ ቢሮው በሚያዘጋጀው ቅፃ ቅጽ መሠረት በቀበሌው ውስጥ የሚኖሩ አርሶአደሮችን ወይም አርብቶ አደሮችን ስም ዝርዝር ከእያንዳንዳቸው የመሬት ይዞታ መጠን ወይም የእንስሳት ብዛት መጠን ጋር በየዓመቱ ተጨማሪ ግብር ከፋዮችን በማካተት ከመስከረም 30 በፊት ለወረዳው አስተዳደር የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

፬፥ የተወሰነው የግብርና ሥራ ገቢ ግብር እና የመሬት መጠቀሚያ ክፍያ በወረዳ አስተዳደር ም/ቤት ፀድቆ ሲተላለፍለት ዝርዝሩን በቀበሌው ጽ/ቤት በመለጠፍ ለሕብረተሰቡ ግልጽ ማድረግ አለበት፡፡

፭፥ ለተቀበለው ገንዘብ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ለእያንዳንዱ አርሶና አርብቶ አደር የመስጠት እና የተሰራባቸውን ደረሰኞችን ሙሉ በሙሉ ሰብስቦ እንዳጠናቀቀ ለወረዳው ፋይናንስ ጽ/ቤት ተመላሽ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

፮፥ ከእንዳንዱ አርሶና አርብቶ አደር ላይ የተሰበሰበውን ገቢ በሙሉ በወሩ ወይም ባጠረ ጊዜ ለወረዳው ገቢዎች ጽ/ቤት በደረሰኝ ገቢ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

፯፥ በአሰባሰብ ሂደትም ለተቀበለው ገንዘብ ለዘርፉ ተለይቶ የተዘጋጀውን የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ለእያንዳንዱ ከፋይ የመስጠት እና የተሰራባቸው

forums, so that farmers and pastoralists can understand and properly implement the obligations imposed by the proclamation.

2. Shall verify and submit the landholding size or the cattle ownership size data that declared by every farmer and pastoralist to the Woreda Administration.

3. Shall notify the woreda administration before September 30 of the list of names of farmers or pastoralists living in the kebele along with the size of each land holdings or the number of livestock, each year including additional taxpayers with the form prepared by the Bureau,

4. It shall post on the kebele office and clarify to the community the agricultural income tax and land use fees approved by the woreda administration council,

5. It shall issue a revenue collection receipt to each farmer for the money received and return it to the woreda finance office upon completion of the full collection of the receipts for which it was made.

6. It shall submit the revenue collected from every farmer and pastoralist on the basis of receipt to the woreda revenue office during a month or a shorter period of time.

7. It shall give a distinct receipt to the tax payer on the collection process and return to the full used

ደረሰኞች በሙሉ ወዲያውኑ ለወረዳው ተመላሽ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

፰÷ በዚህ አዋጅ በተጣለበት ግዴታ መሠረት የመሬት ይዞታው መጠን ወይም የእንስሳት እርባታው ብዛት በተወሰነው የጊዜ ገደብ ያላስታወቀ ወይም አሳንሶ ያስታወቀ አርሶ ወይም አርብቶ አደር በቀበሌው ቢኖር የጊዜ ገደቡ በተጠናቀቀ በ15 ቀናት ጊዜ ውስጥ የቀበሌ ገማች ኮሚቴ በማዋቀር የክፍያውና የግብሩ መሠረት ተገምቶ እንዲቀርብ የማድረግ ሥልጣንና ግዴታ አለበት፡፡

፱÷ ማንኛውም አርሶ ወይም አርብቶ አደር የተወሰነለትን የገቢ ግብር እና የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ በዚህ አዋጅ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ያልከፈለ እንደሆነ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ክስ በመመስረት እንዲከፈል ያደርጋል፡፡

receipts pads to the woreda.

8. It shall have the power and obligation to set up a kebele assessment committee within 15 days of the end of the deadline and make an estimate of the basis of the fees and taxes when a farmer or a pastoralist who does not declare or underestimate the amount of land holdings or the number of livestock in accordance with the obligations imposed by this Proclamation.

9. Shall file a lawsuit on a court with a jurisdiction whenever a farmer or pastoralist fails to pay the specified income tax and land use fees within the time limits provided for in this Proclamation.

## ፲፮. የወረዳ አስተዳደር ተግባርና ኃላፊነት

፩÷ በተለያዩ የሕዝብ ም/ቤት ጉባኤዎች እና የሕዝብ መድረኮች የአዋጁን አስፈላጊነትና አላማ ለሕብረተሰቡ፣ ለቀበሌ አመራሮችና ለሕዝብ ተወካዮች በማሳወቅ በአዋጁ የተጣለባቸውን ግዴታዎች ተገንዝበው የሚጠበቅባቸውን በአግባቡ እንዲፈጽሙ ማስቻል ይኖርበታል፡፡

፪÷ በቀበሌ አስተዳደር ተዘጋጅቶ የቀረበለትን የእያንዳንዱን አርሶ ወይም አርብቶ አደር የይዞታ መጠን ወይም የእንስሳት ብዛት ልክ ትክክለኛነቱን አመሳክሮ በማረጋገጥ መረጃውን ለወረዳው የገቢዎች ጽ/ቤት ወዲያውኑ በማስተላለፍ ከእያንዳንዱ አርሶ ወይም አርብቶ አደር የሚፈለገውን የገቢ ግብር እና የመሬት መጠቀሚያ ክፍያ መጠን በወቅቱ እንዲወሰን ያደርጋል፡፡

፫÷ በገቢዎች ጽ/ቤት ተወስኖ በየቀበሌው ተለይቶ የቀረበለትን ከእንዳንዱ አርሶ ወይም አርብቶ

## 16. Power and Functions of Woreda Administration

1. It shall aware the rationale and the objective of the proclamation for the society, Kebele administrator, and peoples' representatives using various public council assemblies and public forums to enable them to comprehend the duties of each deployed in the proclamation.

2. Shall verify and confirm the payment base data received from Kebele administration and transfer to the woreda revenue office so that the due income tax and land use fee amount of every farmer or pastoralist will be assessed on time.

3. Shall verify and approve the income tax and land use fee assessment done by the woreda revenue

| | |
|---|---|
| አደር የሚፈለገውን የገቢ ግብር እና የመሬት መጠቀሚያ ክፍያ መጠን መረጃ መርምሮ በማጽደቅ በዚሁ መሠረት እንዲሰበሰብ በየዓመቱ ከመስከረም 30 በፊት ለየቀበሌው አስተዳደር ያስተላለፋል፡፡ | office that every farmer or pastoralist required to pay annually before September 30 E.C of the year so that collection to be effected accordingly. |
| ፬፥ የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የግብርና ሥራ ገቢ ግብር በዚህ አዋጅ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ በቀበሌው አስተዳደር መሰብሰቡን እና ገንዘቡንና የተሠራባቸውን ደረሰኝ ጥራዞች ለግብር አስገቢው መ/ቤት በወቅቱ ገቢ መደረጉን የመከታተልና የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡ | 4. Shall have the responsibility to follow and supervise whether the tax collectors have been undertaking the proper collection of the income tax and land use fee and submit the money and the used receipt pads to the Woreda revenue office on time. |
| ፭፥ የሚፈለግባቸውን የግብርና ስራ ገቢ ግብር እና የመሬት መጠቀሚያ ክፍያ በወቅቱ ሳይከፍሉ የቀሩ አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች የቀበሌው አስተዳደር ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት በማቅረብ ከነመቀጫው እንዲከፍሉ ማድረጉን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፡፡ | 5. Shall supervise and ensure whether the kebele administration enforced the defaulters to effect the due income tax and use fee, by charging them at a court with jurisdiction. |
| **፲፯. የቢሮው ተግባርና ኃላፊነት** | **17. Duties and Responsibilities of the Bureau** |
| ፩፥ በዚህ አዋጅ መሠረት በክልሉ አርሶና አርብቶ አደር ላይ የተጣለው የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የግብርና ሥራ ገቢ ግብር አወሳሰንና አሰባሰብ በሕጉ መሠረት መፈፀሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡ | 1. Shall monitor and control the assessment and collection of rural land use fee and agricultural activities income tax that levied on farmers and pastoralists by as per the law. |
| ፪፥ ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የሚረዱ መመሪያዎችና የመረጃ መሰብሰቢያ፣ ማጠናቀሪያ ማስተላለፊያ ቅፃቅፆች እና መዛግብቶች ያዘጋጃል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፡፡ | **2.** Shall prepare directives, formats for data collection, consolidation and transferring to implement the proclamation; and follow ups the implementations. |
| ፫፥ ከወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤት ተረጋግጦ የሚተላለፍለትን በየቀበሌው ተለይቶ የተዘጋጀው የመሬት ይዞታ ስፋት እና የእንስሳት እርባታ ሃብት ብዛት ዝርዝር መረጃ መሠረት በማድረግ በአንቀጽ 6፣ 8 እና 9 እንደተደነገገው | **3.** Shall compute and assess the income tax and the use fee requirements of every farmer or the income tax of every pastoralist based of every kebele on the farmers landholding and the |

| | |
|---|---|
| ከእያንዳንዱ አርሶ አደር የሚፈለገውን የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር እና ከእያንዳንዱ አርብቶ አደር የሚፈለገውን የእንስሳት እርባታ ገቢ ግብር መጠን በመወሰን ዝርዝር መረጃዉን በየቀበሌው አዘጋጅቶ ለወረዳው አስተዳደር ም/ቤት ከመስከረም 15 በፊት ያስተላልፋል፡፡ | pastoralists cattle ownership size data, that confirmed by the woreda administrative council, in accordance with Article 6, 8 and 9; and shall transfer to Woreda Council before September 24 G.C. |
| ፬÷ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የተዘጋጀው የክፍያና የግብር መሠረት የሆነው መረጃና ከእያንዳንዱ አርሶና አርብቶ አደር በየዓመቱ መከፈል የሚገባው የመጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ስራ ገቢ ግብር መጠን መረጃ የሚያዝበትና ክትትል የሚደረግበት ቋሚ መዝገብ የማዘጋጀትና በየቀበሌው ለይቶ የመመዝገብ ግዴታ አለበት፡፡ | **4.** Shall have the obligation to keep a book record of the use fee and agricultural income tax of every farmers and pastoralists as per tax base and payment data prepared according to sub article 3 of this article. |
| ፭÷ በክልሉ ፋይናንስ ቢሮ ተለይቶ የተዘጋጀው የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያንና የግብርና ሥራ ገቢ ግብር መሰብሰቢያ ደረሰኝ ሥርጭትና አመላለስ መረጃ በመያዝ ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፡፡ | **5.** Shall hold and follow ups the data on dispatch and return of the income tax and the land use fee receipt pad prepared for this purpose by the Regional Finance Bureau. |
| ፮÷ በቀበሌው አስተዳደር ከቀበሌው አርሶ ወይም አርብቶ አደሮች የሰበሰበውን የክፍያና የግብር ገንዘብ ስለትክክለኛነቱ አረጋግጦ በደረሰኝ በመቀበልና በተገቢው የገቢ ሂሣብ ኮድ በመመዝገብ ለወረዳው ፋይናንስ ጽ/ቤት በደረሰኝ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡ | 6. Shall verify, ensure and receive the land use fee and income tax collected from the farmers or pastoralists by kebele administration and record on appropriate revenue code and transfer to the woreda Finance Office. |
| ፯÷ እያንዳንዱ አርሶና አርብቶ አደር የከፈለውን የግብር መጠን ከቀበሌው በሚደርሰው የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ 2ኛ ቅጂ ላይ የሰፈረው መረጃ በመዝገብ በማወራረስ የአሰባሰቡን ሕጋዊነትና ትክክለኛነት ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፡፡ | 7. Shall monitor and validate the proper performance of tax collection by triangulating the data available in the 2nd copy of used receipt pad, delivered by the kebele administration tax payment reciept. |
| ፰÷ በወቅቱ ያልከፈሉ አርሶና አርብቶ አደሮችን በመለየት ዝርዝር መረጃውን አዘጋጅቶ ሥልጣን | 8. Shall select and list out the farmers and pasturalists who failed to pay in the due date and |

ላለው ፍ/ቤት ቀርበው በሕግ አስገዳጅነት ከነመቀጫው እንዲከፍሉ እንዲደረግ ለወረዳውና ለቀበሌ አስተዳደር ያስተላልፋል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፡፡

፱፥ ይህን አዋጅና አዋጁን ተከትሎ በሚወጡ ደንብና መመሪያዎች አፈፃፀም ላይ ለወረዳው እና ለቀበሌ አስተዳደር አካላት ተገቢው የግንዛቤ ማስጨበጫ በመስጠት በሕጉ የተጣለባቸውን ኃላፊነት እንዲፈጽሙ ይደግፋል፣ ይከታተላል፡፡

## ፲፰. የፋይናንስ ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት

በየደረጃው የሚገኙ ፋይናንስ ቢሮ ቅርንጫፎች፡-

፩፥ የገጠር መሬት መጠቀሚያና እርሻ ሥራ ገቢ ግብር መሰብሰቢያ ደረሰኞችን በወቅቱ በበቂ ሁኔታ እንዲታተም ያደርጋል፡፡

፪፥ የገጠር መሬት መጠቀሚያና የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር መሰብሰቢያ ደረሰኞችን ለቀበሌ አስተዳደሮች አስፈርሞ ያሰራጫል ፣ይከታተላል፣

፫፥ የተሰራባቸው የገጠር መሬት መጠቀሚያና የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር መሰብሰቢያ ደረሰኞችን ፈርመው ከወሰዱ አካላት ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ ይረከባል፤ ይከታተላል፡፡

፬፥ ተሰርቶባቸው የተመለሱ የገጠር መሬት መጠቀሚያና የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር መሰብሰቢያ ደረሰኞችን ኦዲት በማድረግ የተሰበሰበውን ገቢ ትክክለኛነቱን ያረጋግጣል፣ ጉድለት ካለ ያስመልሳል፡፡

## ፲፱. ደረሰኝ ስለመስጠት

እያንዳንዱ አርሶ ወይም አርብቶ አደር በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚፈጽመው ክፍያ ከግብር ሰብሳቢው ሕጋዊ ደረሰኝ ወዲያውኑ የማግኘት መብት አለው፡፡

transfer the data to the kebele and woreda administration to sue them in a court having jurisdiction.

9. Shall provide awareness for the kebele and woreda administrative bodies to enable them to act on their powers and functions stipulated by this law; monitor and support their implementation of this proclamation, regulation, and directives.

## 18.Duties and Responsibilities of Finance Bureau

Branches of the Finance Bureau at all levels:-

1. Ensure the rural land use and agricultural income tax collection receipts are adequately printed in a timely manner.
2. Dispatches and follows the signed rural land use and farming collection receipts to the local administrations.
3. Hand over by monitoring the validity of the used receipt pads from the entities that have signed and received the tax collection receipts.
4. Audit the used and returned revenue collection receipts of rural land use and farming activities; recover if there is a deficiency.

## 19. Providing Receipt

Every farmer or pastoralist has the right to get a receipt from the tax collector for his tax payment forthwith.

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፳. በኤሌክትሮኒክስ ዘዴዎች ስለመጠቀም

ቢሮው በዚህ አዋጅ እና በአዋጁ መሠረት በሚወጣው ደንብ መሠረት የተቋሙን ተግባራትን ዉጤታማ እና ቀልጣፋ እንዲሆኑ የሚያጠናክር አሰራር ሥርዓት፣ የመረጃ አስተዳደር፣ አደረጃጀትና ልውውጥ ሥርዓትን ይበልጥ ቀልጣፋ እና ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችሉ የኤሌክትሮኒክስ ዘዴዎች በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፡፡

### ፳፩. ነጻ ስለማድረግ

ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው በሰንጠረዥ 6 የተመለከቱት ከገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ እና ከግብርና ሥራ ገቢ ግብር ነጻ ተደርገዋል፡፡

### ፳፪. ስለመቀጫ

፩÷ ማንኛውም አርሶ ወይም አርብቶ አደር በዚህ አዋጅ የተጣለበትን ግዴታ በመተላለፍ የመሬት ይዞታውን መጠን ወይም የእንስሳት እርባታውን ብዛት በወቅቱ በቀበሌው ለአስተዳደር ሳያሳውቅ ከቀረ ወይም አሳንሶ ካስታወቀ ባላስታወቀው ወይም አሳንሶ ባስታወቀው የይዞታ መጠን ወይም የእንስሳት እርባታው ብዛት አንፃር መክፈል የሚገባውን የመሬት መጠቀሚያ ክፍያና የግብርና ሥራ ገቢ ግብር ላይ 5% በመቀጫ በተጨማሪነት ይከፍላል፡፡ ሆኖም የመቀጫው መጠን የመሬት መጠቀሚያ ክፍያውንና የግብርና ሥራ ገቢ ግብሩን መብለጥ የለበትም፡፡

፪÷ ማንኛውም አርሶ አደር ወይም አርብቶ አደር በዚህ አዋጅ መሠረት ሊከፍል የሚገባውን የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የግብርና ስራ ገቢ ግብር በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሳይከፍል ከቀረ ክፍያው ወይም ግብሩ

## Part Five

## Miscellaneous Provisions

### 20. About using electronic Methods

The Bureau shall, by virtue of this proclamation and the regulations issued pursuant to it, establish a system of procedures that will strengthen the effectiveness and effiecency of institution's activities; and shall widely utilize automated technologies that will make the information management, organization, and exchange system more effiecient and effective.

### 21. Exemption

Those referred to in Table 6 in connection with this proclamation are exempt from rural land use fees and agricultural income tax.

### 22. penalty

1. Any farmer or pastoralist, who violates the duty to timely declare the actual land holding size or number of cattle owned, shall pay the penalty of 5% percent to the additional income tax and use fee on undeclared or under declared payment base. However, the amount of the fine should not exceed the land use fee and agricultural income tax that he has declared or underestimated.
2. Any farmer or pastoralist who fails to pay, within the period specified by this proclamation, the income tax or the rural land use fee imposed on him in accordance with this proclamation, shall not excced to penalty of two percent (2%)

በዘገየበት የሚጣለው በእያንዳንዱ ወር የክፍያውንና የግብሩን ሁለት በመቶ /2 በመቶ/ መብለጥ የለበትም፡፡

፫፦ ከቀበሌው ግብር ከፋይ ነዋሪዎች የሰበሰበውን ግብር እና የመጠቀሚያ ክፍያ እንዲሁም የተሰበሰበበት ደረሰኝ በወቅቱ ለወረዳው የፋይናንስ ጽ/ቤት ገቢ ሳያደርግ ወይም ሳያቀርብ የቀረ የቀበሌ አመራር አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፬፦ የቀበሌ አመራሩ የሰበሰበውን የመሬት መጠቀሚያ ክፍያና የግብርና ሥራ ገቢ ግብር እስከ ግንቦት 30 ገቢ ካላደረገ ክፍያው በዘገየበት ለመጀመሪያው ወር ወይም በከፊል ለሆነው ጊዜ 5%/ አምስት በመቶ/ እና ከሁለተኛ ወር ጀምሮ ለእያንዳንዱ ተጨማሪ ወር ወይም በከፊል ጊዜ ደግሞ 2% /ሁለት በመቶ/ ቅጣት እንዲከፍል ይደረጋል፡፡ ዝርዝር አፈጻጸሙ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ፳፫. ወለድ

የቀበሌ አመራሩ የሰበሰበውን የመሬት መጠቀሚያ ክፍያና የግብርና ሥራ ገቢ ግብር እስከ ግንቦት 30 ገቢ ካላደረገ ክፍያው ለዘገየበት ባለፈው ሩብ ዓመት በንግድ ባንኮች ስራ ላይ በዋለው ከፍተኛ የማበደሪያ ወለድ ምጣኔ መሰረት ወለድ ይከፍላል፡፡ ዝርዝር አፈጻጸሙ ፋይናንስ ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ፳፬. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ወይም የመንግሥት ተቋም ይህንን አዋጅ እና በአዋጁ መሠረት የሚወጣውን ደንብና መመሪያ የማክበርና የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

## ፳፭. ማበረታቻ አበል ክፍያ

የቀበሌ አስተዳደር በዚህ አዋጅ መሠረት ከቀበሌው ግብር ከፋይ ነዋሪዎች ከሚሰበሰበው ጠቅላላ የመሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር ገንዘብ ውስጥ ሁለት በመቶ (2%) በኮሚሽን መልክ ይከፈለዋል፡፡

of the amount of tax and use fee in respect of every month.

3. Any kebele administration which fails to deliver or provide the collected tax and fee and the used receipt pad to the woreda finance office in the due period shall be criminaly liable.

4. If the Kebele administrator fails to pay the land use fees and agricultural income tax collected up to May 30, he will pay a penalty of 5% / five per cent/ for the first month or part of the period in which the payment is delayed and 2% / two per cent for each additional month or part of the period from the second month onwards.

## 23. Interest

The kebele administrator fails to submit the rural land use fee and agricultural actities income tax, collected up to the 7th date of June, shall pay additional interest of the highest loan interest rate of the quarter of the Commercial Bank last year interest rate. The details shall be determined by a directive to be issued by the Bureau of Finance.

## 24. Duty to Cooperate

Any individual or legal person or government organization shall have the obligation to cooperate in the carrying out of this proclamation, the due regulation and directives.

## 25. Remuneration of Service Motivation

Every kebele administration shall be paid two percent (2%) as commission from the total collected income tax and land use fee amount from the kebele tax payer residents.

**፳፮. የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የገቢ ግብር ነጻ የማድረግ ስልጣን**

በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ቀበሌዎች በሚገኙ አርሶ አደሮች ወይም አርብቶ አደሮች ላይ በድርቅም ሆነ ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች በምርታቸው ላይ ጉዳት ቢደርስ የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት የመሬት መጠቀሚያ ክፍያና የገቢ ግብር በሙሉ ወይም በከፊል እንዳይከፍሉ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

**፳፯. ስለ ወንጀል ቅጣት**

፩÷ ይህንን አዋጅ ወይም በአዋጁ መሠረት የሚወጣውን ደንብ ወይም መመሪያ የተላለፈ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው በወንጀል ሕግ መሠረት ይቀጣል፡፡

፪÷ ከቀበሌው አርሶ አደር ወይም አርብቶ አደር የመሬት መጠቀሚያ ክፍያና የግብርና ሥራ ገቢ ግብር እንዲሁም የተሰበሰበበትን ደረሰኝ በወቅቱ ለወረዳው ገቢዎች ጽ/ቤት ገቢ ሳያደረግ ወይም ሳያቀረብ የቀረ የቀበሌ አመራር የወንጀል ህግ ይቀጣል፡፡

**፳፰. የታክስ አስተዳደር አዋጅ ተፈጻሚነት**

በዚህ አዋጅ ባልተሸፈኑ የታክስ አስተዳደር ጉዳዮች ላይ አግባብነት እስካላቸው ድረስ የክልሉ ታክስ አስተዳደር አዋጅ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

**፳፱. ደንብ የማውጣት ስልጣን**

፩÷ የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የሚረዳውን ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡

፪÷ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ /1/ መሰረት የሚወጣዉን ደንብ ለማስፈጸም ቢሮው ዝርዝር

**26. Power to exempt rural land use fees and income tax**

Where the harvest of farmers or pastoralists of one kebele or more is adversely affected by drought or the force measures, the farmers or pastoralists may totally or partially be waived by the regional Executive council from paying the land use fee, agricultural income tax and income tax on cattle rearing due on them. The details shall be determined by the regulation.

**27. Criminal Penalties**

1. Any person who violates the provisions of this proclamation or regulation and directives to be issued in pursuance of this proclamation shall be punishable in accordance with the criminal code.
2. The kebele leadership that fails to pay or submit the land use fee and agricultural income tax collected from the kebele farmers and pastoralists, as well as the receipts collected, to the woreda revenue office on time, shall be punished under the criminal law

**28. Application of Tax Administration Proclamation**

The provisions of the Regional Tax Administration Proclamation shall apply to tax administration matters not covered by this Proclamation, to the extent that they are relevant.

**29. Power to issue regulations**

1. The executive Council may issue regulation for by implementation of this proclamation.
2. The Bureau may issue directives for the implementation of regulations issued pursuant to

መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፴. መሸጋገሪያ ድንጋጌ

ቀድሞ በወጡ ሕጎች የተሰጡ ውሳኔዎች፣አሠራሮች እና በእንጥልጥል ላይ የሚገኙ ጉዳዮች ከዚህ አዋጅ ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ በዚህ አዋጅ እውቅና አግኝተው ተፈጻሚነታቸው ይቀጥላል፡፡

## ፴፩. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጐች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ደንብ፣መመሪያ እና ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## ፴፪. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ ከፀደቀበት ታህሳስ ፭ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አርባ ምንጭ ታህሳስ ፭ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

**ጥላሁን ከበደ**

**የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት**

**ርዕሰ መስተዳድር**

sub Article (1) of this Article.

## 30. Transitory Provision

Decisions rendered, procedures established and matters pending under previous Laws shall be enforced and remain valid under this Proclamation, provided that they are consistent with this Proclamation.

## 31. Inapplicable laws

Any proclamation, regulation, directive and customary practice inconsistent with this proclamation shall not apply to matters covered by this Proclamation.

## 32. Effective Time of the Proclamation

This proclamation shall come into force on, December 15, 2023, upon its approval by the South Ethiopia Regional State Council.

Done at Arba minch, 15th of December 2023

**Tilahun Kebede**

**President of South Ethiopia Regional State**

## አባሪ

### ሰንጠረዥ 1

የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ ተመን (በምግብ ዋስትና ያልታቀፈ አርሶ አደር)

| ተ.ቁ | መሬቱ የዋለበት አላማ | የመሬት መጠቀሚያ ክፍያ |
|---|---|---|
| 1 | **ለእርሻና ለእንስሳት ልማት የዋለ መሬት** | **ብር በሄክታር** |
| 1. | ለእርሻና ለእንስሳት ልማት የዋለ መሬት | 300 |
| 2 | **ለባህር ዛፍ ምርት የዋለ የዋለ መሬት** | **ብር በሄክታር** |
| 2.1. | ለባህር ዛፍ ምርት የዋለ የዋለ መሬት | 400 |
| 3 | **ለሌሎች ተግባራት የዋለ** | **ብር በሄክታር** |
| 3.1 | **ለሌሎች ተግባራት የዋለ መሬት** | 300 |

## Appendix

### Table 1
### Rural Land Use Fee rate (Food Insecure Farmer)

| No | **purpose of the land** | **Land Use Fee** |
|---|---|---|
| 1 | Land used for agriculture and livestock cultivation | birr per Hectare |
| 1.1. | Land used for agriculture and livestock cultivation | 300 |
| 2 | Land used for eucalyptus production | birr per Hectare |
| 2.1. | Land used for eucalyptus production | 400 |
| 3 | Used for other activities | birr per Hectare |
| 3.1 | Land used for other activities | 300 |

## ሰንጠረዥ 2

### የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ ተመን (በምግብ ዋስትና የታቀፈ አርሶ አደር)

| ተ.ቁ | መሬቱ የዋለበት አላማ | የመሬት መጠቀሚያ ክፍያ |
|---|---|---|
| 1 | **ለእርሻና ለእንስሳት ልማት የዋለ መሬት** | **ብር በሄክታር** |
| 1.1. | ለእርሻና ለእንስሳት ልማት የዋለ መሬት | 150 |
| 2 | **ለባህር ዛፍ ምርት የዋለ መሬት** | **ብር በሄክታር** |
| 2.1. | ለባህር ዛፍ ምርት የዋለ መሬት | 200 |
| 3 | **ለሌሎች ተግባራት የዋለ መሬት** | **ብር በሄክታር** |
| 3.1 | ለሌሎች ተግባራት የዋለ መሬት | 200 |

## Table 2

### Rural Land Use Payment rate (Food Security Embraced Farmer)

| No | **purpose of the land** | **Land Use Fee** |
|---|---|---|
| 1 | Land used for agriculture and livestockcultivation | (birr per Hectare) |
| 1.1. | Land used for agriculture and livestock cultivation | 150 |
| 2 | Land used for eucalyptus production | (birr per Hectare) |
| 2.1. | Land used for eucalyptus production | 200 |
| 3 | Used for other activities | (birr per Hectare) |
| 3.1 | Land used for other activities | 200 |

## ሰንጠረዥ 3

### ለኢንቨስትመንትና ለንግድ ሥራ ለዋለ መሬት የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ ተመን

| ተ.ቁ | መሬቱ የዋለበት አላማ | የመሬት መጠቀሚያ ክፍያ ብር (ብር በሄክታር) |
|---|---|---|
| 1 | **ለእርሻና ለእንስሳት ልማት የዋለ መሬት** | |
| 1.1 | የእርሻ መሬቱ ከማዕከላዊ ገበያ(አዲስ አበባ) ያለው ርቀት 400 ኪ.ሎ ሜትር በታች | 1000 |
| 1.2 | መሬቱ ከማዕከላዊ ገበያ(አዲስ አበባ) ያለው ርቀት 401-600 ኪ.ሎ ሜትር | 900 |
| 1.3. | መሬቱ ከማዕከላዊ ገበያ(አዲስ አበባ) ያለው ርቀት 601 ኪ.ሎ ሜትር በላይ | 700 |
| 1.4 | መሬቱ የመንግስት ልማት ድርጅቶች (የአከባቢው ልማት ማህበር ከሆነ | 500 |
| 2 | **ለማኑፋክቸርንግ** | |
| 2.1. | የእርሻ መሬቱ ከማዕከላዊ ገበያ(አዲስ አበባ) ያለው ርቀት 400 ኪ.ሎ ሜትር በታች | 2500 |
| 2.2. | መሬቱ ከማዕከላዊ ገበያ(አዲስ አበባ) ያለው ርቀት 401-600 ኪ.ሎ ሜትር | 2000 |
| 2.3. | መሬቱ ከማዕከላዊ ገበያ(አዲስ አበባ) ያለው ርቀት 601 ኪ.ሎ ሜትር በላይ | 1500 |

## Table 3

### Rural land use fee rate for land used for investment and commercial purposes

| No | purpose of the land | Land use fee: (birr per hectare ) |
|---|---|---|
| 1 | **Land used for agriculture and livestock cultivation** | |
| 1.1 | Distance of agricultural land from Central Market (Addis Ababa) less than 400 kilometers | 1000 |
| 1.2 | Distance of the land from Central Market(Addis Ababa): 401-600 kilometers | 900 |
| 1.3. | The land is located over 601 kilometers from the Central Market (Addis Ababa) | 700 |
| 1.4 | If the land belongs to the State Development Corporation (Local Development Association) | 500 |
| 2 | **Manufacturing** | |
| 2.1. | Distance of agricultural land from Central Market (Addis Ababa) less than 400 kilometers | 2500 |
| 2.2. | Distance of the land from Central Market(Addis Ababa): 401-600 kilometers | 2000 |
| 2.3. | The land is located over 601 kilometers from the Central Market (Addis Ababa) | 1500 |

| | | |
|---|---|---|
| 3 | **ለአገልግሎት** | |
| 3.1 | የእርሻ መሬቱ ከማዕከላዊ ገበያ(አዲስ አበባ) ያለው ርቀት 400 ኪሎ ሜትር በታች | 2000 |
| 3.2 | መሬቱ ከማዕከላዊ ገበያ(አዲስ አበባ) ያለው ርቀት 401-600 ኪሎ ሜትር | 1500 |
| 3.3 | መሬቱ ከማዕከላዊ ገበያ(አዲስ አበባ) ያለው ርቀት 601 ኪሎ ሜትር በላይ | 1200 |
| 4 | **ለሌሎች ዘርፎች** | |
| 4.1. | የእርሻ መሬቱ ከማዕከላዊ ገበያ(አዲስ አበባ) ያለው ርቀት 400 ኪሎ ሜትር በታች | 1500 |
| 4.2. | መሬቱ ከማዕከላዊ ገበያ(አዲስ አበባ) ያለው ርቀት 401-600 ኪሎ ሜትር | 1300 |
| 4.3. | መሬቱ ከማዕከላዊ ገበያ(አዲስ አበባ) ያለው ርቀት 601 ኪሎ ሜትር በላይ | 1100 |

## ሰንጠረዥ 4
## የግብርና ሥራ ገቢ ግብር ተመን

| ተ.ቁ | ገቢው የተገኘበት ሥራ | የግብርናሥራ ገቢ ግብር |
|---|---|---|
| 1 | ከእርሻ ስራ ገቢ በዝናብ ውሃ በመጠቀም ለሚያመርት | በሄክታር በብር 200 |
| 2 | ከእርሻ ስራ ገቢ በባህላዊ መስኖ | በሄክታር በብር 250 |

| | | |
|---|---|---|
| 3 | **For service** | |
| 3.1 | Distance of farmland from Central Market (Addis Ababa) less than 400 kilometers | 2000 |
| 3.2 | Distance of the land from Central Market(Addis Ababa): 401-600 kilometers | 1500 |
| 3.3 | The land is located over 601 kilometers from the Central Market (Addis Ababa) | 1200 |
| 4 | **For other sectors** | |
| 4.1. | Distance of agricultural land from Central Market (Addis Ababa) less than 400 kilometers | 1500 |
| 4.2. | Distance of the land from Central Market(Addis Ababa): 401-600 kilometers | 1300 |
| 4.3. | The land is located over 601 kilometers from the Central Market (Addis Ababa) | 1100 |

## Table 4
## Agricultural activity income tax rate

| No | Activity from which the income earned | Income tax of Agricultural activity |
|---|---|---|
| 1 | Income from farming which is generated by the use of rainwater | per hectare birr 200 |
| 2 | Income from farming which is used for traditional irrigation | per hectare birr 250 |

| | | |
|---|---|---|
| | በመጠቀሚ ለሚያመርት | |
| 3 | ከእርሻ ሥራ ገቢ በዘመናዊ መስኖ በመጠቀም ለሚያመርት | በሄክታር በብር 300 |
| 4 | ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው የግብርና ምርቶች | ሄክታር በብር 400 |

| | | |
|---|---|---|
| 3 | For those who use modern irrigation to earn income from farming | per hectare birr 300 |
| 4 | High Value Agricultural Products | per hectare birr 400 |

## ሰንጠረዥ 5

## ከእንስሳት እርባታ የሚገኝ ገቢ ግብር ማስከፈያ ተመን

| ተ.ቁ | ከእንስሳት እርባታ የሚገኝ ገቢ ግብር | ለአርሶ አደር | ለአርብቶ አደር በብር |
|---|---|---|---|
| 1 | ከፍየልና በግ | ለእያንዳንዱ ብር 15 | 10 |
| 2 | ግመል | ለእያንዳንዱ ብር 200 | 200 |
| 3 | ቀንድ ከብት | ለእያንዳንዱ ብር 50 | 30 |
| 4 | ጋማ ከብት | ለእያንዳንዱ ብር 100 | 50 |

## Table 5

## Income from animal husbandry taxation rate

| No | Income from animal husbandry | For farmer | For pastoral birr |
|---|---|---|---|
| 1 | Goat and sheep | 15 birr for each | 10 |
| 2 | Camel | 200 birr for each | 200 |
| 3 | Cattle | 50 birr for each | 30 |
| 4 | Pack animal (gamma cattle) | 100 birr for each | 50 |

| ሰንጠረዥ 6<br>**ከግብርና ሥራ ገቢ ግብር ነጻ የተደረገ ገቢ** | **Table 6**<br>**Income exempt from agricultural income tax** |
|---|---|
| ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ከግብርና ሥራ ገቢ ግብር ነጻ ተደርገዋል፡-<br>1. ከ0.25 ሄክታር በታች በሆነ የገጠር መሬት የሚጠቀም አርሶ አደር ከግብርና ሥራ ግብር ነጻ ተደርገዋል፣<br>2. በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ከብር 7,200/ሰባት ሺህ ሁለት መቶ ብር/ በታች ግብርና ሥራ ገቢ የሚያገኝ አርብቶ አደር ከግብርና ሥራ ገቢ ግብር ነጻ ተደርጓል፣<br>3. በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ከተከናወኑ ከሚከተሉት የእንስሳት ዕርባታ የሚገኝ ገቢ ከግብርና ሥራ ገቢ ግብር ነጻ ተደርገዋል፣<br>ሀ. እስከ 15 በግና ፍየል ዕርባታ<br>ለ. እስከ 5 ግመል ዕርባታ<br>ሐ. እስከ 10 ቀንድ ከብት ዕርባታ<br>መ. እስከ 5 ጋማ ከብት ዕርባታ | The following are exempted from agricultural income tax:<br>1. A farmer using rural land of less than 0.25 hectares is exempted from agricultural work income tax;<br>2. A pastoralist whose annual income is below Birr 7,200 / seven thousand two hundred Birr shall be exempted from agricultural work income tax;<br>3. Income from the following livestock farming activities carried out within a year shall be exempted from agricultural income tax:<br>a) Up to 15 sheep and goat breeding<br>b) Up to 5 camel breeding<br>c) Up to 10 cattle breeding<br>d) Up to 5 pack animal (gamma cattle) herds |